የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
የምርጫ ጉዳዮች
አንደኛ ይግባኝ ችሎት

የይግባኝ መዝገብ ቁጥር 216104 እና 215703

መጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም.

ዳኞች፡-1. ሙስጠፋ አህመድ
2. ቀነዓ ቂጣታ
3. ብርሃኑ መንግሥቱ

ይግባኝ ባዮች፡-

1. ብልጽግና ፓርቲ - ተወካይ የጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት/በመዝገብ ቁጥር 216104/ ተወካይ ሳሲይታደስ ቀረቡ
2. አቶ ልዑልሰገድ አሺኖ ክንፌ
3. ወ/ሮ ሀሳቤ አደም አቢኖ
4. አቶ አስቻለው ቡባ ባልቻ
5. አቶ ሁሴን አባቴ ቡሼ

} ቀረቡ
በመዝገብ ቁጥር የቀረበ የለም
215703 ቀረቡ

መልስ ሰጪ፡-

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ /በሁለቱም መዝገቦች/ - ተወካይ ወንጌል አባተ ቀረቡ

ተጨማሪ መልስ ሰጪዎች፡-

1. አቶ ልዑልሰገድ አሺኖ ክንፌ - ቀረቡ
2. ወ/ሮ ሀሳቤ አደም አቢኖ - የቀረበ የለም
3. አቶ አስቻለው ቡባ ባልቻ } በመዝገብ ቁጥር 216104 - ቀረቡ
4. አቶ ሁሴን አባቴ ቡሼ - ቀረቡ
5. አቶ እንዳልካቸው አወል ሁሴን ቀረቡ
6. ብልጽግና ፓርቲ - ተወካይ የጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት /በመዝገብ ቁጥር 215703/

ቁጥራቸው 216104 እና 215703 በሆኑ መዝገቦች የቀረበው ይግባኝ ከስር አንድ ውሳኔ የመነጨ በመሆኑ በአንድነት ተጣምሮ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል።

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 4-8-14

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
የምርጫ ጉዳዮች
አንደኛ ይግባኝ ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 216104 እና 215703

# ፍ ር ድ

በሁለቱም መዝገቦች ለቀረበው የይግባኝ ክርክር መነሻ የሆነው በ20/01/2014 ዓ.ም. በተከናወነው ድጋሚ ምርጫ በመስቃን እና ማረቆ 02 ምርጫ ክልል ከሚገኙ 106 የምርጫ ጣቢያዎች መካከል በቁጥር በተጠቀሱ የተለያዩ የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ ሂደት ተከስተዋል በተባሉ ጥሰቶች እና ጥፋቶች ምክንያት የምርጫው ውጤት እንዲሰረዝ የግል ተወዳዳሪዎች የነበሩት የመዝገብ ቁጥር 215703 ይግባኝ ባዮች በ25/01/2014 ዓ.ም. አዘጋጅተው ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ቦርዱ ጉዳዩን በማስረጃ ማጣራቱን እና በተለይ በ22ቱ የምርጫ ጣቢያዎች የጎላ ችግር የተከሰተ መሆኑ መረጋገጡን ገልጾ የመስቃንና ማረቆ 02 ምርጫ ክልል የድጋሚ ምርጫ ውጤት እንዲሰረዝ በ01/02/2014 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡

በዚህ የቦርዱ ውሳኔ ላይ የመዝገብ ቁጥር 216104 ይግባኝ ባይ የሆነው የጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲ በ02/03/2014 ዓ.ም. አዘጋጅቶ ያቀረበው አራት ገጽ የይግባኝ ቅሬታ አጭር ይዘት፡-

1. የምርጫው ውጤት በምርጫ ጣቢያና በምርጫ ክልል ደረጃ የተገለጸ ሆኖ ሳለ በምርጫ፣የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155 /1-6/ በተመለከተው መሠረት በምርጫ ጣቢያ እና በምርጫ ክልል ደረጃ የቀረበ ቅሬታ ሳይኖር ተገቢ ሂደቶችን ዘሎ በቀጥታ የቀረበለትን አቤቱታ ቦርዱ ተቀብሎ በማስተናገድ ውሳኔ የሰጠው አለአግባብ ነው፣
2. ቦርዱ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የምርጫ ውጤቱ መሰረዝ የሚመለከታቸውን በምርጫ ሂደቱ የተሳተፉ ፓርቲዎች ተገቢ መከራከሪያዎችን እና ማስረጃዎችን ማቅረብ እንዲችሉ መብት እና ዕድል መስጠት ሲገባው የአንድ ወገን አቤቱታና ማስረጃ መርምሮ የምርጫ ውጤቱን በመሰረዝ ውጤቱን ማሳወቁ ተገቢ አይደለም፣

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 4-8-14

3. ቦርዱ የምርጫ ውጤቱ እንዲሰረዝ ውሳኔ የሰጠው የቀረበለትን ማስረጃ በአግባቡ ሳይመዝን እና ጉዳዩን ከሚመለከታቸው ሶስተኛ ወገኖች ሳያጣራ ነው፣
4. ቦርዱ የምርጫ ውጤቱን ለመሰረዝ የሚያስችል በቂ ማስረጃ አግኝቻለሁ ቢል እንኳ አሳማኝ ማስረጃ ቀርቦባቸዋል ያላቸውን የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ውጤት ብቻ መሰረዝ ሲገባው የ106 ቱንም የምርጫ ጣቢያዎች ውጤት ሰርዞ ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ የወሰነው አለአግባብ ነው፣

በመሆኑም የቦርዱ ውሳኔ ተሽሮ የምርጫ ውጤቱ ትክክለኛ ነው ተብሎ ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቋል።

ችሎቱም የይግባኝ ቅሬታው መርምሮ መልስ ሰጪው መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም. በመስቃንና ማረቆ ምርጫ ክልል 2 የተደረገውን ምርጫ በተመለከተ የኢትዮጵያ የምርጫ አዋጅን እና መመሪያን የሚጥሱ ተግባራት መፈጸማቸው ተረጋግጦአል በሚል ምክንያት የምርጫ ክልሉ የምርጫ ውጤት እንዲሰረዝ እና ድጋሚ ምርጫ እንዲከናወን ሲወስን የግል ዕጩ ተወዳዳሪዎች ጥሰቶቹን ፈጽሞአል ብለው የጠቀሱት የብልጽግና ፓርቲ በመሆኑ ፓርቲው በምርጫ ክልሉ በተካሄደው ምርጫ ተሳታፊና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በገለጸው የምርጫ ውጤት አሸናፊ መሆኑ ሲታይ መልስ ሰጪ በዚህ ጉዳይ ውሳኔ ከማሳለፉ በፊት ይግባኝ ባዩ በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን፣መከላከያ እና መከራከሪያዎቹን እንዲያቀርብ ሳያደርግ የመወሰኑን አግባብነት በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት፣በምርጫ አዋጅ እና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ከመሰማት፣ከመከራከር እና ፍትሕ ከማግኘት መብት አንጻር መልስ ሰጪው ባለበት አጣርቶ ለመወሰን እንዲያስችለዉ ይግባኙ ለክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ እና ተጨማሪ መልስ ሰጪዎቹም በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 32/2 እና 40/2 በተመለከተው መሰረት በይግባኙ ገብተው እንዲከራከሩ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።

በቦርዱ ውሳኔ ላይ የመዝገብ ቁጥር 215703 ይግባኝ ባዮች የሆኑት እነ አቶ ልዑልሰገድ አሺኖ ክንፌ /አራት ሰዎች/ በ23/02/2014 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት አራት ገጽ የይግባኝ ቅሬታ አጭር ይዘት፦

1. በምርጫ ክልሉ ከሚገኙ 106 የምርጫ ጣቢያዎች መካከል ችግር ተከስቶባቸዋል ተብለው በቦርዱ የተለዩት 22 የምርጫ ጣቢያዎች ብቻ ሆኖ ሳለ ቦርዱ ምንም ቅሬታ ያልቀረበባቸውን 84 የምርጫ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 1-8-14

ጣቢያዎች የምርጫ ውጤት አብሮ በመሰረዝ ውሳኔ የሰጠው ከተጠየቀው ዳኝነት ውጪ በመሆኑ ውሳኔው ሽሮ የ22ቱ የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ውጤት ተሰርዞ በ84ቱ የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫው አሸናፊ እንዲለይ ተብሎ ውሳኔ ይሰጥልን፣

2. ምርጫው እንዲደገም እና በዚህም ምክንያት የአገር ሀብትና ጉልበት እንዲባክን ባደረጉ አካላት በተለይም በገዢው ፓርቲ አመራሮች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያቀረብነውን የይግባኝ ቅሬታ ነጥብ ቦርዱ በዝምታ ያለፈው አለአግባብ በመሆኑ በዚህ ረገድ ውሳኔው ታርሞ ተገቢው ውሳኔ ይሰጥልን፣

የሚል ሲሆን የይግባኝ ቅሬታው ተመርምሮ መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም. በመስቃንና ማረቆ ምርጫ ክልል 2 በተደረገው ምርጫ በምርጫ ክልሉ ሥር ካሉት 106 የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በ22ቱ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ የኢትዮጵያ የምርጫ አዋጅን እና መመሪያን የሚጥሱ ተግባራት ተፈጽመዋል በማለት ይግባኝ ባዮች ያቀረቡትን ቅሬታ ተከትሎ መልስ ሰጪ ጉዳዩን በማጣራት ባሳለፈው ውሳኔ በእነዚህ የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ሕጉን የሚጥሱ ተግባራት መፈጸማቸው ተረጋግጧል ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ቅሬታ በቀረበባቸው ምርጫ ጣቢያዎች ብቻ ሳይሆን ቅሬታ ያልቀረበባቸውን 84 ምርጫ ጣቢያዎች ጨምሮ አጠቃላይ የምርጫ ክልሉ ውጤት እንዲሰረዝ እና ድጋሚ ምርጫ እንዲከናወን የመወሰኑን አግባብነት መልስ ሰጪው ባለበት አጣርቶ ለመወሰን እንዲቻል ይግባኙ ለክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ እና ተጨማሪ መልስ ሰጪውም በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 32/2 እና 40/2 በተመለከተው መሰረት በይግባኙ ገብቶ እንዲከራከሩ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ፍርድ ቤትም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. የመዝገብ ቁጥር 216104 ይግባኝ ባይ የሆነው የጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት በራሱ ስም ይግባኝ ለማቅረብ የሚያስችል መዋቅራዊ ብቃት የለውም በማለት መልስ ሰጪ ያቀረበው የመቃወሚያ ክርክር ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
2. በሁለቱም መዝገቦች መልስ ሰጪው በይግባኝ ደረጃ በዚህ ፍርድ ቤት የቆጠረውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ እንዲሁም የመዝገብ ቁጥር 216104 ይግባኝ ባይ የሆነው የብልጽግና ፓርቲ - ተወካይ



ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ቀን 4-8-14

የሆነዉ የጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ከይግባኝ ቅሬታው ጋር በማይያያዝ በመዝገብ ቁጥር 216104 የቆጠረውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ በዚህ የይግባኝ መዝገብ መስማት አስፈላጊ ነው ወይስ አይደለም?

3. መልስ ሰጪው የመዝገብ ቁጥር 216104 ይግባኝ ባይ የሆነውን የጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት በመልስ ሰጪነት ወደ ክርክሩ ሳይጋብዝ የምርጫ ክልሉ የምርጫ ውጤት እንዲሰረዝ ውሳኔ መስጠቱ የምርጫ ሕጉን እና የሥነ ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም በማለት ይግባኝ ባይ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
4. መልስ ሰጪ ሙሉ የምርጫ ክልሉን የምርጫ ውጤት ሰርዞ ምርጫው በ106ኙም የምርጫ ጣቢያዎች እንዲደገም መወሰኑ የሚነቀፍ ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ ይግባኙ የቀረበበት ውሳኔ ጉድለት ያለበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር እንደሚከተው መርምሮአል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ</u>፡-የጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት (መዋቅራዊ ብቃት) የለውም በማለት መልስ ሰጪው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መቃወሚያ ያቀረበው ሕጋውያን መስፈርቶችን አሟልቶ በቦርዱ የተመዘገበው እና በዚህም ምክንያት ሕጋዊ ሰውነት ያገኘው ብልጽግና ፓርቲ እንጂ የፓርቲው የክልል እና የዞን መዋቅር ጭምር ባለመሆኑ ይግባኝ ባይ የጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት በራሱ ስም መክሰስም ሆነ መከሰስ አይችልም በማለት ነው፡፡ይግባኝ ባይ ለመቃወሚያው ባሰማዉ ክርክር የፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብ ለክልል እና ለዞን የብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤቶች በራሳቸው ስም መክሰስ እና መከሰስ እንደሚችሉ የሚፈቅድ ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡ይህንኑ ለማጣራት ብልጽግና ፓርቲ በምዝገባ ጊዜ ለምርጫ ቦርድ አቅርቦ ያስመዘገበውን የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ ይግባኝ ባይ እና መልስ ሰጪው ከቀጠሮ በፊት አቅርበው ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ እንዲያደርጉ ፍርድ ቤቱ በ20/05/2014 ዓ.ም. ትዕዛዝ ሰጥቶአል፡፡ሆኖም በትዕዛዙ መሠረት ከሁለቱም መወገኖች ቀርቦ የተያያዘ መተዳደሪያ ደንብ የለም፡፡በሌላ በኩል ግን የመስቃንና ማረቆ 02 ምርጫ ክልል የምርጫ ውጤት ስረዛን በተመለከተ በፍርድ ቤት ያለውን ጉዳይ መከራከር እንዲችል የብልጽግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት በቁጥር ብፓ/ምዘ1/869/14 በ17/06/2014 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ለደቡብ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት የሰጠውን ውክልና እና እና የክልሉ ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ደግሞ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 4-8-14

በተራው በቁጥር ደ/ብ/07685 በ18/06/2014 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ለጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሰጠውን ውክልና ቅጂ ይግባኝ ባዩ በ22/06/2014 ዓ.ም. ከተጻፈ መግለጫ ጋር አቅርቦ አያይዟል፡፡ይህም የመዝገብ ቁጥር 216104 ይግባኝ ባይ የሆነው የጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ከብልጽግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ጀምሮ በተዋረድ በተሰጠው የሥልጣን ውክልና መሰረት በዚህ መዝገብ ያቀረበውን ይግባኝ ዋናዉን የብልጽግና ፓርቲ በመወከል መምራት የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በዚህ መነሻነት ፍርድ ቤቱ የጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይግባኝ ያቀረበዉና በክርክሩ በመልስ ሰጭነት የተሳተፈዉ በራሱ የሕግ ሰዉነት ኖሮት ሳይሆን በአገራዊዉ የብልጽግና ፓርቲ በተሰጠዉ የዉክልና ሥልጣን መነሻ ነዉ እንደሆነ ተገንዘበናል፡፡በእርግጥ ይግባኙን ሲያቀርብ እና በመልስ ሰጭነት በክርክሩ ሲሳተፍ ከአገራዊ ፓርቲዉ የተሰጠዉ ዉክልና ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ አለመኖሩ እንደጉድለት የሚታይ ቢሆንም በዚህ ጉድለት መነሻ (በአሁኑ ጊዜ ዉክልና ተሰጥተቶ እያለ) ዉክልና ሳይኖረዉ ያቀረበዉ ይግባኝ ነዉ ብሎ ክርክሩን ወደኋላ የሚመልስ ድምዳሜ ላይ መድረስ ከምርጫ ጉዳይ ክርክር ባህርይ እና ከሥነ ሥርዓት ሕጉ ዓላማ ጋር ስለማይሄድ ጉዳዩን ከዚህ አንጻር በመመልከት ከዚህ ረገድ በመልስ ሰጭ የቀረበዉን መቃወሚያ አልተቀበልንም፡፡በዚህ ፍርድ ላይ የተመለከተዉ አሰያየምም ይህንን ታሳቢ ያደረገ ነዉ፡፡

<u>ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ</u>፡-የመዝገብ ቁጥር 216104 ይግባኝ ባይ የሆነው የብልጽግና ፓርቲ ተወካይ የሆነዉ የጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት እና መልስ ሰጪው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በየክርክር አቋማቸው መሰረት ለማስረዳት በይግባኝ ደረጃ በርካታ ምስክሮችን እና የሰነድ ማስረጃዎችን ቆጥረዋል፡፡ይግባኙ ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በምርጫ፣የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155 (4) ድንጋጌ መሠረት ሲሆን ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ቅሬታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር ውሳኔ መስጠት እንደሚገባዉ በዚሁ ድንጋጌ ስር ተመልክቶአል፡፡ ይሁን እንጂ ማስረጃን አስቀርቦ መመርመር ማለት በይግባኝ ደረጃ በተከራካሪ ወገኖች የተቆጠረውን ምስክር እና ሰነድ በሙሉ አስቀርቦ መስማት እና መመርመር ማለት ብቻ አይደለም፡፡ከማስረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ሥነ ሥርዓታዊ መርህ አንጻር ፍርድ ቤቶች በይግባኝ ደረጃ ማስረጃ አስቀርበው የሚሰሙት እና የሚመረምሩት አንድም አስፈላጊነቱ የሚታመንበት ከሆነ አሊያም ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ በታየበት ጊዜ ማስረጃ ያልተሰማ ከሆነ ነው፡፡

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ቀን 4-8-14

በተያዘው ጉዳይ መልስ ሰጪው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ምስክሮችን በመስማት እና ሰነዶችን በመመርመር ተገቢውን ማጣራት አድርጓል።የምስክሮቹን ቃል እና የሰነዶቹን ይዘት ቦርዱ በውሳኔ ላይ አስፍሯል።በዚህም ሁኔታ ቦርዱ የሰማቸው ምስክሮች እና የተቀበላቸው ሰነዶችሌይግባኝ ክርክሩን መርምሮ ለመወሰን በቂ ሆነው በመገኘታቸው በተከራካሪ ወገኖች በይግባኝ ደረጃ የተቆጠሩትን ምስክሮች አስቀርቦ መስማቱን እና ሰነዶችን አስቀርቦ መመርመሩን ለጉዳዩ አወሳሰን ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘውም።

<u>ሶስተኛውን ነጥብ በተመለከተ</u>፡-ቦርዱ የምርጫ ውጤቱን የሰረዘው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 በአንቀጽ 7 (በቦርዱ ውሳኔ ላይ በስህተት አንቀጽ 6 በሚል የተጠቀሰ) በንዑስ አንቀጽ 20 እና የምርጫ፣የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎችን በአስረጂነት በመጥቀስ ነው።የምርጫ፣የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 10 ድንጋጌ ድጋሚ ምርጫ ሊካሄድ የሚችልበትን አግባብ የሚያመለክት ጥቅል ድንጋጌ ሲሆን ቦርዱ በምርጫ ሂደት የምርጫ ውጤትን የሚያዛንፍ የህግ ጥሰት ተከስቷል ብሎ ሲያምን ውጤቱን የመሰረዝ እና ድጋሚ ምርጫ የማካሄድ ሥልጣን እና ተግባር የተሰጠው ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7 (20) ድንጋጌ ያመለክታል።ቦርዱ በምርጫ ሂደት የምርጫ ውጤትን የሚያዛንፍ የህግ ጥሰት ተከስቷል ወይም አልተከሰተም ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችሉትን ፍሬ ነገሮች ማጣራት የሚገባው ምን ዓይነት የማጣራት ሥርዓትን ተከትሎ ስለመሆኑ አዋጁ የሚያስቀምጠው መስፈርት የለም።በርግጥ ከምርጫ እና ከምርጫ ውጤት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች የተለያዩ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና የሕብረተሰብ ክፍሎችን ተነጻጻሪ ጥቅሞች የሚመለከቱ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም።ይህ ማለት ግን ሁል ጊዜ ቦርዱ ጉዳዩን አጣርቶ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ወገኖች በሙሉ ጠርቶ ክርክራቸውን እና ማስረጃዎቻቸውን እንዲያሰሙ የማድረግ ግዴታ አለበት ማለት አይደለም።የምርጫ ሕጎቹ በዚህ ረገድ የሚጥሉት ግዴታ ካለመኖሩም በላይ ከምርጫ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በመሠረታዊ ባህሪያቸው ፍትሐብሔራዊ ቢሆኑም ቦርዱ የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች ሲሰማ፣ማስረጃዎችን ሲመረመር፣ ማስረጃዎችን ሲመዝን እና ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራርም ሆነ የማስረጃ አቀባበልና ምዘና ሥርዓት አስፈላጊነቱን ሲያምን ተግባራዊ ማድረግ



ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
4-8-14

ከሚችል በስተቀር ልክ እንደፍርድ ቤት በጥብቅ ዲሲፕሊን የሥነ ሥርዓት ሕጉን ድንጋጌዎች እንዲከተል አዋጅ ቁጥር 1133/2011ም ሆነ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አያስገድዱትም:: ይህ ማለት ግን ቦርዱ በከፊል የዳኝነት ነክ አካል (quasi judicial organ) ጭምር መሆኑን ታሳቢ ባደረገ መልኩ በአዋጆቹ እና አዋጆቹን ተከትለዉ በወጡ መመሪያዎች የተመለከቱትን በጉዳዩ ጥቅም ያላቸዉ ወገኖች ያላቸዉን መሰረታዊ እና ሥነ ሥርዓታዊ መብቶቻቸዉን (Substantive and procedural rights) ታሳቢ አድርጎ በገለልተኛነት በራሱ መንገድ ጉዳዩን ማጣራት የለበትም ማለት አይደለም::ይህም ቦርዱ ከአንድ ወገን የቀረበለትን አቤቱታ መነሻ አድርጎ በሚያደርገው ማጣራት የምርጫ ውጤቱን ሊያፋልሱ የሚችሉ ድርጊቶች መከሰታቸውን በሕጉ ከተሰጠው ሥልጣን እና ተግባር አንጻር ለራሱ በሚያሳምን ሁኔታ ማረጋገጥና ያጣራውን ፍሬ ነገር መሠረት አድርጎ በገለልተኛነት አስተዳደራዊ ባህርይ ያለዉን ውሳኔ የሚሰጥ ከመሆኑ በቀር በጉዳዩ ተነጻጻሪ መብት ያላቸውን ሌሎች ወገኖች ወደ ክርክሩ በመጋበዝ አከራክሮና ማስረጃዎቻቸዉን ሰምቶና መዝኖ እንዲወስን በሕግ የተጣለበት ግዴታ አለመኖሩን መገንዘብ የሚያስችል ነው::የመዝገብ ቁጥር 216104 ይግባኝ ባይ የሆነው የብልጽግና ፓርቲ - ተወካይ የሆነዉ የጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት የሚከራከረው በምርጫ ሂደቱ ላይ የምርጫውን ውጤት ሊያዛንፍ የሚችል ምንም ዓይነት ችግር አልተከሰተም በማለት ሳይሆን ይልቁንም ችግሮች መከሰታቸውን በከፊል አምኖ ነገር ግን የሚከራከረው የችግሩ ባለቤት ወይም ምንጭ የብልጽግና ፓርቲ - ተወካይ የሆነዉ የጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲ ሳይሆን ይልቁንም የግል ተወዳዳሪዎች እራሳቸው ናቸው በማለት መሆኑን የቅሬታው ይዘት ያመለክታል:: በመሠረቱ ቦርዱ በምርጫው ሂደት የምርጫውን ውጤት ሊያፋልሱ የሚችሉ ክስተቶች መታየታቸውን አረጋግጦ የምርጫ ውጤቱ እንዲሰረዝ ከመወሰን በቀር ችግሮቹ እንዲከሰቱ የተደረገው ከተከራካሪ ወገኖች በአንደኛዉ አማካይነት እንደሆነ በውሳኔው ላይ አልገለጸም::ይህም ማለት ለተከሰቱት ችግሮች የጉራጌ ዞን ብልጽግና ፓርቲንም ሆነ የግል ተወዳዳሪዎቹን ኃላፊ አላደረገም::በእርግጥ ቦርዱ በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7/20 በመጨረሻዉ ዐረፍተ ነገር ላይ በተመለከተዉ መሰረት የሕዝብ ሀብት(ገንዘብ የሰዉ እና የጊዜ ሀብት) ባክኖ የተደረገዉን ድጋሚ ምርጫ ዉጤት እንዲሰረዝ የሚያደርግ የሕግ ጥሰት እና የሰላምና ጸጥታ ችግር እንዲሁም የማጭበርበር ድርጊት የፈጸሙ ሰዎችን ለይቶ በሕግ እንዲጠየቁ አለማድረጉ እንደጉድለት የሚታይ ነዉ::በምርጫ ሂደቱ ላይ የምርጫውን ውጤት ሊያዛንፉ የሚችሉ ክስተቶች መፈጠራቸው በከፊልም ቢሆን በይግባኝ ባይ ጭምር የሚታመንበት እስከሆነ እና ለችግሮቹ መከሰት ኃላፊ የተደረገ የተለየ ወገን እስከሌለ ድረስ ቦርዱ በክርክሩ ሂደት ብልጽግና ፓርቲን አለማሳተፉ



ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 4-8-14

በፓርቲው መብትና ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሷል ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም መልስ ሰጪው የመዝገብ ቁጥር 216104 ይግባኝ ባይ የሆነውን የብልጽግና ፓርቲ በመልስ ሰጪነት ወደ ክርክሩ ሳይጠራ የምርጫ ክልሉ የምርጫ ውጤት እንዲሰረዝ ውሳኔ መስጠቱ የምርጫ ሕጉን እና የሥነ ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም በማለት ይግባኝ ባይ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>አራተኛውን እና የመጨረሻውን ነጥብ በተመለከተ</u>፡-በመስቃን እና ማረቆ 02 ምርጫ ክልል የሚገኙት 106 የምርጫ ጣቢያዎች ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል ቦርዱ ችግር ተከስቷል ያለው በ22ቱ ላይ ብቻ ሆኖ እያለ ከ22ቱ የምርጫ ጣቢዎች ጋር የቀሪዎቹን 86 የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ውጤት ቦርዱ አብሮ መሰረዙ ተገቢ አይደለም በማለት ሁለቱም ወገኖች ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ይሁን እንጂ የቅሬታ ነጥቦቻቸው የተለያዩ ናቸው፡፡የግል ተወዳዳሪዎቹ የቅሬታ ነጥብ ችግር ተከስቶአል የተባለው በ22 የምርጫ ጣቢያዎች በመሆኑ የ22ቱ የምርጫ ጣቢያዎች ውጤት መሰረዝ ተገቢ ሆኖ ነገር ግን ድጋሚ ምርጫ ማድረግ ሳያስፈልግ ችግር ያልተከሰተባቸው የ86 ምርጫ ጣቢያዎች ውጤት የሁሉም ማለትም የ106ቱ የምርጫ ጣቢያዎች ውጤት እንደሆነ ተወስዶ የአጠቃላይ የምርጫ ክልሉ ውጤት ሊገለጽ እና አሸናፊው ሊለይ ይገባል የሚል ሲሆን የጉራጌ ዞን ብልጽና ፓርቲ የቅሬታ ነጥብ ደግሞ የምርጫ ውጤትን የሚያዛንፍ ችግር ተከስቶባቸዋል ከተባሉት 22 የምርጫ ጣያዎች ውጪ በቀሪዎቹ 84 የምርጫ ጣቢያዎች የቀድሞው ውጤት ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባው ከመሆኑ በቀር በ84 የምርጫ ጣቢያዎች ምርጫው ሊደገም አይገባም የሚል ነው፡፡የግል ተወዳዳሪዎቹ በይግባኝ አቤቱታቸው ላይ ቦርዱ ችግር ተከስቷል ያለው በ22ቱ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ብቻ ነው ይበሉ እንጂ በቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ ላይ በመሙላት ለቦርዱ ባቀረቡት ቅሬታ ላይ ውጤትን ሊያፋልስ የሚችል ድርጊት ተፈጽሟል በሚል የገለጹት በ38 እና 39 የምርጫ ጣቢያዎች መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ቦርዱም ቢሆን በሰጠው ውሳኔ ላይ በተለይ በተጠቃሾቹ 22 የምርጫ ጣቢያዎች ላይ የጎላ ችግር የነበረ መሆኑን መረዳቱን ከመግለጹ በቀር በቀሪዎቹ የምርጫ ጣያዎች የተከሰተ ችግር የለም በሚል የደረሰበት ድምዳሜ የለም፡፡ይህም ደረጃው የተለያየ ይሁን እንጂ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ችግሮች የነበሩ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡የግል ተወዳዳሪዎቹ እንደሚከራከሩት የ86 የምርጫ ጣቢያዎችን የመራጮች ድምጽ እንደ 106 የምርጫ ጣቢያዎች (እንደ አንድ የምርጫ ክልል) የመራጮች ድምጽ አድርጎ በመውሰድ የምርጫ ክልሉን የምርጫ



ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ቀን 4-8-14

ውጤት መግለጽ እና የምርጫ ክልሉን አሸናፊ መለየት ዉጤቱ በተሰረዘባቸዉ ጣቢያዎች ዉስጥ በመራጭነት የተመዘገቡ ዜጎችን የመምረጥ እና በሚወክሏቸዉ ሰዎች በፌዴራል እና በክልል ምክር ቤቶች የመወከል መብትን የሚጋፋ በመሆኑ ሕገ መንግሥታዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡የግዝፈቱ መጠን ይለያይ እንጂ የምርጫ ውጤትን የሚያፋልሱ አድራጎቶች የተከሰቱት በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ምርጫው ሊደገም የሚገባው ሙሉ በሙሉ በምርጫ ክልል ደረጃ እንጂ በከፊል አይደለም፡፡በመሆኑም መልስ ሰጪ ሙሉ የምርጫ ክልሉን የምርጫ ውጤት ሰርዞ ምርጫው በ106ቱም የምርጫ ጣቢያዎች (በምርጫ ክልል ደረጃ) እንዲደገም መወሰኑ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ይግባኙ የቀረበበት የቦርዱ ውሳኔ በዉጤት ደረጃ ሲታይ ጉድለት ያለበት ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የመስቃንና ማረቆ 02 ምርጫ ክልል የድጋሚ የምርጫ ውጤት እንዲሰረዝ እና ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በ01/02/2014 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7/20 እና በምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155 (4) የተደነገገዉን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት በአብላጫ ድምጽ ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ቅጂ ለግራ ቀኙ ይሰጥ፡፡
3. ጉዳዩ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/አ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
... ግልባጭ
ቀን 4-8-14